በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/ማ/ቅ/ጅ/ዩ/ቴ/ኢ/ግ/ጉባዔ

ትዕይንት 1

(መጋረጃው ሲከፈት መድረክ ላይ አንድ አባት ሲጸልዩ ይታያል፤ ጸሎታቸውን ሲጨርሱ ወጣት ልጅ ወደርሳቸው ይመጣል)

ወጣቱ፡- አባቴ ሰላም አደሩ እንዴት ኖት

አባት፡- እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ፡ እንዴት ነህ አንተ

ወጣት፡- ደህና ነኝ አባ ምን እሆናለው ብለው ነው.... **(ይተክዛል)**

አባት፡- ልጄ ምነው ደክሞሀል መሰለኝ ና ወደቤት እንግባ ዝናቡም ሊዘንብ ነው ተነስ፤ (ወደቤት ይገባሉ).... አረፍ በል ልጄ

ወጣት፡- እሺ አባዬ አረፍ እላለው..

አባት፡- ያዝ እሰስኪ የእመቤታችንን ጸበል ጸዲቅ..... ልጄ ዛሬ ልክ አይደለህም ምነው ምን ሆንክብኝ?

ወጣት፡- አይ ምንም አልሆንኩም..

አባት፡- የሆነ ነገርማ ሆነሃል፤ ምንድነው ንገረኝ ባይሆን መፍትሄ እንፈልግለታለን

ወጣት፡- አባቴ ሁሉም ነገር አስጠልቶኛል ልመንን ነው!

አባት፡- ልመንን ነው? ማለት?

ወጣት፡- በቃ ልመንን ነው፤ ሰዉ መሬቱ ዕፅዋቱ አራዊቱ ሁሉም ጠልተዉኛል ዉሸታም ናቸው፡ ማንም የሚታመን የለም

አባት፡- ምን እያልከኝ ነው ልጄ ግራ አጋባኸኝ እኮ.... የተፈጠረውን ነገር ለምን በግልጽ አትነግረኝም?

ወጣት፡- አባቴ ከልቤ የማምነው ጓደኛዬ የኔ ነው የምለው ወንድሜ ካደኝ፤ ምስጢሬን በአደባባይ ዘራው፤ ባዶ አረገኝ፡፡...

አባት፡- ባዶ አረገኝ? እንዴት?

ወጣት፡- ምን እንዴት አለው አባ? ካሁን በኋላ ከሰው ጋር መኖር አልፈልግም! ጭው ያለ በረሀ ውስጥ ብቻዬ መኖር ነው ምፈልገው!!!

አባት፡- በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አይ ልጄ ገና ለገና ከጓደኛዬ ጋር ተጣላሁ ብለህ ነው በረሀ ምትሄደው? ልጄ ብቸኝነት መፍትሄ አይሆንም ከራስህ ጋር ከተፈጥሮ ጋር አትስማማም፤ ከተጣላሀቸው ጋር ከልታረቅክ ፈጣሪም አይታረቅህም፤ ውስጥህ ሰላም ካልሆነ ብቸኝነት ጭንቀት ይሆንብሀል፡፡ እናም ልጄ አስተውል ስትደሰት ቃል አትግባ ስታዝን ደግሞ አትከፋ፡፡

ወጣት፡- ካልሆነ እዚሁ ከርሰዎ ጋር ልኑር.....

እኔስ አርሴማን እወዳታለው

አባት፡- ይሸላል ብለኽ ነው? አንድ ታሪክ ልንገርህ፤ ከ10 ዓመት በፊት በጣም የሚዋደዱ ሁለት ጓደኛማቾች ነበሩ፤ እና እነዚህ ሁለት ጓደኛማቾች..... እየሰማኸኝ ነው ልጄ? ምን አልኩህ?

ወጣት፡- አዎ እየሰማሁ ነው፡ በጣም የሚዋደዱ ሁለት ጓደኛማቾች ነበሩ...

አባት፡- አዎ በደንብ ስማኝ! ሁለቱም በጣም ይዋደዱ ነበር ከልጅነታቸው ጀምሮ አፈር ፈጭተው ጭቃ አቡክተው ነው ያደጉት፤ ሲሄዱ አንድ ላይ ሲበሉ አንድ ላይ ሁሉንም ነገር አንድ ላይ ነበር የሚያደርጉት፡፡ ስማቸው ኤፍሬም እና ያሬድ ይባላሉ፤ ኤፍሬም የድሀ ነለልጅ ነው ከእናቱና ከእህቱ ጋር በደሳሳ ጎጆ ውስጥ በፍቅር ይኖራሉ፡፡ ጓደኛው ያሬድ ደግሞ ደህና ገቢ ያላቸው ሲሆን እናቱና አባቱ ግን እጅግ በጣም ይቆጣጠሩተል፤ በተለይ ደግሞ ከኤፍሬም ጋር እንዳይሆን ያስጠነቅቁታል፤ የያሬድ አባት በጣም ጨካኝ ስለነበር ያሰውን ከማረግ ወደኋላ አይልም፤ ኤፍሬምን ብዙ ቀን ያስፈራራው ነበር፡፡ እናም ኤፍሬም በትምህርቱ በጣም ጎበዝ ስለነበር ቀን ትምህርቱን እየተማረ ከትምህርት ሲለቀቁ ደግሞ ሊስትሮ እየሰራ በሚያገኘው ገንዘብ የእርሱንና የቤተሰቡን ወጪ ይደግፋል፤ እና ኤፍሬም....... **(የኤፍሬም ትዕይንት ይጀምራል)**

ኤፍሬም ፡- ማኪ ሂሳብ ደብተሬን አይተሽዋል

ማከዳ፡- ኧረ አላየሁም፡፡ እስቲ እረጋ ብለህ ፈልገው

ኤፍሬም፡- ይ....ኸው አገኘሁት፤ እሺ ካልሲዬን አይተሽዋል

ማከዳ፡- ውይ.. አንተ ሰው ምን ሆነሃል(አብረው ይፈልጋሉ) ይኸውልህ ካሁን በኋላ ምንም እንዳትጠይቀኝ እሺ!

ኤፍሬም ፡- (በእሺታ አንገቱን ነቅንቆ) እኔ የምልሽ ግን ሰሞኑን ት/ቤት አንዷ ዝም ብላ ትከታተለኛለች፤ ክፍላችን እየመጣች ታየኛለች፣ በቃ በምሄድበት ሁሉ እንደ ጥላ ትከተለኛለች

ማከዳ፡- ሃሃሃሃሃ... ማንን አንተን ነው

ኤፍሬም፡- አዎ ምን ይወጣልኛል ቆንጆ ነኝ

ማከዳ፡- አይ ኤፍሬም አስቂኝ ሆነህ የለ እንዴ

ኤፍሬም ፡- በይ በይ አንቺን ከሰሙሽ ብዙ ታወሪያለሽ፤ እ... አሁን እንዴት ነኝ አምሮብኛል ላ??? ምን ዋጋ አለው በመጀመሪያዉ ፔሬድ ሰፖርት አለን በጠዋቱ አንደ ጦስ ዶሮ ሜዳዉን የሯሩጠናል ከዛ ቀኑን ሙሉ ፖሊዮ አንደ ተከተበ ህጻን ልጅ ቁጭ ብዬ እውላለው፤ አንድ እውነት ልንገርሽ ምስጢር ነው ለማንም አትናገሪም?

ማከዳ፡- አዎ አልናገርም

ኤፍሬም፡- ምን መሰለሽ እስከ ዛሬ ድረስ የሮጥኩት ቢለካ ምደርን ሁለት ጊዜ ይከባታል ካላመንሽ ፈተሺኝ፤

ማከዳ፡- ፐፐፐ የኛ ዩሴያን ቦልት አልታወቅክም እንጂ ለካስ ሃይለኛ ሯጭ ነህ

ኤፍሬም፡- ታዲያስ አሁንም የሄን በሚሰጥር የነገርኩሽ ሰፖርት ፌዴሬሽን ከሰማ መቆሚያ መቀመጫ እንዳያሳጡኝ ብዬ ነው

ማከዳ፡- በጣም ይገርማል በል እንካ እንደውም በዛው ፍጥነትህ ይታያል የሁለት ብር ስኳር ገዝተህ ና

ኤፍሬም ፡- (እየሮጠ ይወጣና) ማኪዬ በቃ ብሩን ለግሩፕ ስራ ወሰጄዋለው እሺ... ቻው በቃ

ማከዳ፡- ወይኔ ማከዳ አታለለኝ ማለት ነው ቆይ አገኘው አይደል

ለዳነች፡- ምንድነው ገና በጠዋቱ የምትጨቃጨቁት በሰላም ነው

ማከዳ፡- ምን ባክሽ ይኼ ኤፍሬም ጉድ አድርጎኝ ሄደ፤

ለዳነች፡- ኡኡቴ እሱ ሁሌ አይደል እንዴ የሚሸውድሽ፤ በይ አሁን ሻዩን አፍዪልኝ ለቅሶ አለብኝ ልሄድ ነው

እኔስ አርሴማን እወዳታለው

ማከዳ፡- ሻዩንማ ልጅሽ ይዞት ሄደ

አዳነች፡- ምን አንቺ እንዴት አይነቱ ጨካኝ ነሽ ባክሽ የፈላ ሻይ ይዞ ሲሄድ ዝም ብለሽ አየሽው ለመሆኑ በምንድን ነው የያዘው በፔርሙስ ነው ወይስ

ማከዳ፡- ኧረ እማዬ እንደሱ አይደለም ነገሩ ልጅሽ ኤፍሬም ስኳሩን ይዞት ሄደ አሁንስ?

አዳነች፡- ይዞት ሄደ ሃሃሃሃሃሃ ጉድ እኮ ነው በደንብ አይደል ያታለለሽ. በይ አሁን ያለውን አቅርቢና አመስግነን እንመገብ፤ አኔ የምልሽ ግን እንዴት ነው ሰሞኑን ቤተክርስቲያን እየሄድሽ ጸበሉንስ እየተጠመቅሽ ነው አይደል?

ማከዳ፡- አዎ እማዬ እየሄድኩ ነው ኤፊም እየሄደ ነው፤

አዳነች፡- ጎበዝ ናችሁ እኮ የኔ ልጆች በርቱና ከአባታችሁ የወረሳቹትን የሀይማኖት ትጋት እናንተም ጋር እንዲኖር እፈልጋለው

ማከዳ፡- እሺ እማዬ የአባታችንን ቃልማ መቼም አልረሳውም

አዳነች፡- በጣም ጥሩ በይ ቻው መሄዴ ነው ለቅሶ አለብኝ፤ ኤፍሬም ሲመጣ ምሳዉን ቶሎ አዘጋጅተሽ ስጭው እሺ

ማከዳ፡- እሺ እማዬ እኔ የምልሽ ግን አጎታቸሁን በቅርብ ጊዜ ዉስጥ አስተዋውቀችኋለው ብለሺን ነበር ረሳሺው እንዴ?

አዳነች፡- በፍጹም አልረሳሁትም እንደውም አድራሻውን ስላገኘሁት ዛሬውኑ እቺን ደብዳቤ በፖስታ ቤት ልኬለት እመጣለው፡፡ ቻው..

ማከዳ፡- እሺ ቻው

(አዳነች ትወጣለች ማከዳም ቤቱን እያስተካከለች መጋረጃ ይዘጋል)

ትዕይንት 2

አባት፡- ወ/ሮ አዳነች ከብዙ ዓመታት በኋላ ለ አቶ አበራ በፖስታ ቤት በኩል ደብዳቤ ለከችለት

ወጣቱ፡- ምን የሚል?

(መጋረጃው ሲከፈት አበራ ከቦርሳው ዉስጥ የታሸገ ፖስታ አውጥቶ ያነባል)

«አበራ ደብደቤ ያነባል « ከሁሉም በላይ ሰላመ እግዚአብሔር ይብዛልህ እያልኩኝ ውድ ወንድሜ እንዴት ነህልኝ፤ እኔ በጣም ደህና ነኝ ልጆቼም ደህና ናቸው፤ አንተ ጋርስ ቤተሰቦችህ ሰላም ናቸው?

ወንድሜ ከተለያየን ይኸው ድፍን 15 ዓመት ሆነን አይደል? መለያየት ምን ያክል ከባድ እንደሆነ አውቀዋለው፤ አበራ በአሁን ሰዐት ልጆቼ ስላንተ ነግሬአቸው ሊያገኙህ ይፈልጋሉ... እኔ የምልህ ግን ወንድምአለም ያለፈውን ነገር ይቅር ተባብለን ለመኖር ወስኛለው፤ አንተስ ምን ትለለህ ወንድምአለም?.... እርግጠኛ ነኝ ያንን ባህሪህን እንደተውክ፡ አንተ ባመጣኸው መዘዝ ቤተሰባችን ተበትኗል፣ አንተ በጨርከው እሳት ሁሉም ነገር ተበላሽቷል፡፡ ወንድምአለም አሁን ልወቅስህ ሳይሆን ሁሉን ነገር ረስተን ተገናኝተን እንደድሮአችን እንኑሁን እያልኩህ ነው፤ አሁን ላይ አጠገቤ ከልጆቼ በቀር ወደጅ ዘመድ የምለው ማንም የለም፤ ወንድምአለም ያኔ በህጻንነት ያየሃቸው ሁለቱ ልጆቼ ትልቅ ሆነውልኝል፡ ሰላንተ እየተየቁኝ ስለሆነ እንገናኝ እያልኩህ ነው፤ እሺ እንደምትለኝ ተስፋ አረጋለው..... ባለቤትህን ማርታንም ሰላም በልልኝ፤ መልካም ጊዜ ቻው፡፡»

አበራ፡- የማይታመን!!! አዳነች በህይወት አለሽ ማለት ነው፡፡ ተመስገን ጌታዬ.... ኸረ እንገናኛለን፡ በደንብ ነው ምንገናኘው እህታባዬ

ናፍቀሺኛል፤ ደግሞ ሁለቱ ልጆቿ እንዴት እንደናፍቁኝ...

ማርታ፡- ደህና አደርክ ምነው በጠዋቱ ብቻህን ተወራ ጀመር?

አበራ፡- ባወራም አትፍረጂብኝ በጣም ደስ ብሎኝ ነው!

ማርታ፡- ምን ተገኝቶ ነው ባክህ?

አበራ፡- ሀብት፣ ጸጋ... እህታባን አገኘኋት ደስ አይልም? በጣም ናፍቃኝ ነበር...

ማርታ፡- ደስ ይላል፤

አበራ፡- በጣም እንጂ... ሀገር ወስጥ አለ የተባለ ባል አግብታ ነበር ምትኖረው፤ የነሱን ሀብት ንብረት ማንም ቆጥሮ አይጨርሰውም፡

የፋብሪካው ብዛት ብትዪ፣ ወርቅ ቤት... ምን የሌላቸው አለ??? ባለቤቷ ሞቶ ለብቻዋ እያስተዳደረች የኖረች ነው፤

ማርታ፡- እና ቢኖራቸውስ??

አበራ፡- እንዴ ምን ጥያቄ አለው? ተባብረን እናድጋለና እንበለፅጋለን፤ ላለው ይጨመርለታል ሲባል አልሰማሽም??

ማርታ፡- ይሁንልህ እሺ እኔ የምልህ .... ሰሞኑን መጥፎ መጥፎ ህልም እያየሁ ነው፡፡በጣም ጨንቆኛል

አበራ፡- ወይ ጉድ ያንቺ ህልም ደግሞ ማለቂያ የለው ....

ማርታ፡- እውነቴን እኮ ነው፡ አንተ ምንም አላየህም?

አበራ፡- ማን! እኔ? መች አስተኝተሽኝ ነው የማየው በይ በይ አንቺ ከሰሙሽ እንደ አባይ ወንዝ ማቆሚያ የለሽም፤ የሆነች የምሄድባት

ቦታ አለብኝ.... ቻው

ማርታ፡- አይይ ... እንዲያው ያየሁትን ህልሜን ሳይሰማ ይሄዳል እንዴ፡ ቀረበታ! ያሬድን ጠርቼ ለርሱ እነግረው የለ ያሬድ... አንተ ያሬድ

(ወደ ጓዳ ገብታ ትጠራዋለች)

ያሬድ፡- አቤት እማዬ ጠራሺኝ

ማርታ፡- ዛሬ ምን የመሰለ ህልም አየሁ መሰለህ....... ስማኝማ ልንገርህ

ያሬድ፡- ኡ!!!.... የንቺ ህልም፤ መች ይሆን ህልም ሳታዩ የምትነሺው? እሺ ምን አየሽ ንገሪኝ

ማርታ፡- በትልቅ ሜዳ ላይ እየሄድኩ ይመስለኛል... ዝናቡ ደመናውን ሰማዩን ሸፍኖታል፤ መብረቁ ደግሞ.... ግግው! ...... ዱ.. ዱ ዱ.. ይላል፡፡ ከዚያ ዝም ብዬ እየሄድኩ ከፊቴ ትልቅዬ አንበሳ አይመጣ መሰለህ.....

ያሬድ፡- ህእአ...... ከዚያስ..... አባረረሽ? በላሽ?

ማርታ፡- እስቲ ተረጋጋ.... አንበሳው ጉምልል ጉምልል እያለ መጣ.... እኔ ማርታ ደግሞ ልክ እንደ እቴጌ ጣይቱ ጀንን ብዬ ቆምኩልህ ከዚያ አፉን ከፍቶ ሊበላኝ አ! ሲል

ያሬድ፡- ከዚያስ

ማርታ፡- ከዚያማ እኔ እናትህ አፉን እንደከፈተ አጄን በከፈተው አፍ ከትቼ ጭራወን ያዝኩት፤ ከዚያ ግልብጥ አደረኩትና መሬት ላይ ስጥለው አጄ ላይ ድመት ሆኖ እርፍ አለ

ያሬድ፡- ከዚያስ

ማርታ፡- ምን ከዚያ አለው ብንን ብዬ ተነሳሁ

ያሬድ፡- እንኳንም ነቃሽ እንጂ ተበልተሽ ነበር፡፡ በይ እማዬ ኤፍሬም እየጠበቀኝ ስለሆነ ልሂድ ቶሎ እመጣለሁ

ማርታ፡- ኤፍሬም? ይሄን መናጢ ልጅ እንዳታገኘው አላልኩህም ነበር?

ያሬድ፡- እማዬ - ኤፍሬምንማ እንደዚህ ብለሽ አትሰድቢውም፤ እንደወንድሜ ነው የማየው፤ እማዬ ሁለተኛ ይሄን ቃል እንዳትደግሚው

ማርታ፡- ምን አልክ አንተ?

ያሬድ፡- አዎ! ማንም ምንም እንዲለው አልፈልግም ለጓደኝነት መሰረቱ ደግሞ ገንዘብ ሳይሆን ንፁህ ፍቅር ነው፡፡ ... በቃ ልሄድ ነው

ማርታ፡- አውርተህ ልብህ ውልቅ ብሏል..........

ያሬድ፡- እስኪ አሁን በጠዋቱ ከምትጨቀጭቂኝ የማትፈልጊው ሁለት መቶ ብር ስጪኝና ብን ብዬ ልጥፋልሽ

ማርታ፡- (ከቦርሳዋ አውጥታ ትሰጠዋለች) ቆይ ግን አንተ በየዜው የምትወሰወደውን ብር ምን እያረከው ነው?

ያሬድ፡- ብሩንማ ትልቅ ፎቅ እያሰራሁ ነው ሊያልቅ ትንሽ ይቀረዋል፡፡

ማርታ፡- ኧረ ባክህ!!!...... በል በጊዜ ግባ እሺ የአባትህን ነገር ታውቀው የለ **(ያሬድ ወደ ውጭ ሲወጣ በሩ ላይ ዘበኛው (መኩሪያ)ጋቢ እየቋጨ ያገኘዋል....) መኩሪያ በተፈጥሮ በከፊል ነው የሚሰማው**

መኩሪያ፡- ኧረ ቀስ ወዴት ነው ሩጫው?

ያሬድ፡- ከጓደኛዬ ጋር ቀጠሮ አለኝ እዛ ነው ምሄደው

መኩሪያ፡- ቆጠራ? የምን ቆጠራ ነው አንተዬ?

ያሬድ፡- ቀጠሮ ነው ያልኩህ አትሰማም እንዴ? ባይሆን ማታ ላመሽ ስለምችል አባዬ ሳይሰማ በሩን ቀስ ብለህ ትከፍትልኛለህ

መኩሪያ፡- ብሩን? የምን ብር? መቼ ሰጠኸኝና

ያሬድ፡- ይሄ ሰውዬ ጤና የለውም እንዴ? በሩን! ነው ያልኩህ

መኩሪያ፡- እህ .... እንደዛ ነው ያልከው ችግር የለውም በቃ ግን እንዳታመሽ ምናልባት ለሽ ብዬ ተኝቼ ከሆነ ውጪ ማደርህ ነው፡፡

ያሬድ፡- ቀልደኛ ነህ ባክህ በልቻለሁ(**ይሄዳል**)

መኩሪያ፡- ብላቸው? ማንን ነው ምበላው? ዛሬምን ሆኗል ይሄ ልጅ..... አሄሄ.... ደግሞ ፀሀይዋ ምን ሆና ነው ምታቃጥለው? ነደድን እኮ

አይ ግሎባል ወርሚንግ (global warming) መጋረጃ ይዘጋል፡፡

እኔስ አርሴማን እወዳታለው

ትዕይንት 3

(*መጋረጃው ሲከፈት አባት ተሪካቸውን ለወጣቱ ልጅ ይነግሩታል*)

አባት፡- ማከዳ በጣም ትሁት ልጅ ነበረች፤ በልብ ህመም ምክኒያት ራሷን ስታ ትወድቅ ነበር፡፡ትምህርቷንም ትታዋለች ኤፍሬም ከሚያገኛት ሽርፍራፊ ሳንቲቲ እናቷ የሰውፊት ፊት አይታ እንጨት ለቅማ በምታገኘው ገንዘብ ያሳክሟት ነበር ፡፡ያሬድም እንዲሁ እናትና አባቱ የሻይ ብለው ከሚሰጡት በአቅሙ ይረዳቸዋል ቢሆንም ግን ሳይታሰብ በጠና ሁኔታ ማካዳን ነፍስ ውጪ ነፍስ ግቢ ደረጃ ላይ ደረሰች ህመሙ ሲለው ይመልሳታል አንዳንዴ ደግሞ በድን ያደርጋታል ብቻ የሷነገር እናቷ ዘወትር እንዳስጨነቃት ነበር ...... **(ሲጨርስ ያሬድና ኤፍሬም ተያይዘው ወደቤት ይገባሉ ማከዳ አሟት ተኝታለች እናት አጠገቧ ሆና ታስታምማለች)**

ኤፍሬም፡- ማከዳ ማኪ...... ምነው ምን ሆነሽ በጣም አመመሽ እንዴ?

ያሬድ፡- ማኪ ምን ሆንሽብኝ? አይዞሽ እሺ ደግሞ በጣም ትኩሳት አለሽ፤ ምሳሽን በልተሻል ግን? እቴቴ ምሳ በላች እንዴ

ለዳነች፡- ኧረ ከነጋ ምንም አልቀመሰችም ገና አሁን ነው ከሆስፒታል የመጣነው

ያሬድ፡- እና ምን አሏችሁ? ንገሪኝ እቴቴ አታስጨንቂኝ

ለዳነች፡- ምንም! በቃ ተስፋ የለም! (ታለቅሳለች)

ኤፍሬም፡- ተስፋ የለም ማለት?

ለዳነች፡- በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ውጪ ሀገር ሄዳ እንድትታታከም ወጪው ደግሞ እስከ 500.000 ሺህ ብር እንደ ሆነና ካልሄደች ግን ማከዳ......

ኤፍሬም፡- ማከዳ ምን? ምን ትሆናለች?

ለዳነች፡- ማከዳ ትሞታ....

ኤፍሬም፡- ተይው ተይው አትጨርሺው፡፡ ወይኔ እህቴ ላንቺ መሆን ያቅተኝም ከየትም ከየትም ብዬ አሳክምሻለሁ፡፡

ያሬድ፡- **(በሲቃ ድምፅ)** አምላኬ ሆይ እባክህን ተለመነኝ ማከዳን ፈውሰስልኝ...... እሷን ከምትወስዳት እኔን ሺህ ጊዜ ውሰደኝ እሷን ተውልኝ...... **(ያለቅሳል)**

ኤፍሬም፡- ያሬድ ምን እያልክ እንደሆነ ታውቀሀል? ሞትን እየተመኘህ?

ያሬድ፡- አዎ ለማከዳ የኔ ሞት ሲያንሳት (እንባው እየጠራረገ) ያንተ ብቻ እህት ናት ያለው ማነው የነስ እህት አይደለችም?

ማከዳ፡- ያሬድዬ በቃህ ተወው አታልቅስ ምንም አልሆንኩም እኮ ደህና ነኝ እማዬ እባክሽ ተው በዬው

ለዳነች፡- ተው ተባልክ አይደል እንዴ በቃ አታልቅስ በሉ አሁን በሉ አሁን እጃችሁን ታጠቡና ምሳ ብሉ ተነሱ… ተነሱ.

ኤፍሬም፡- እማዬ አሁን ነው የበላሁት ባይሆን እናንተ ብሉ …… ደግሞ የምነግርሽ ነገር ትልቅ ነገር አለ

ለዳነች፡- ምንድነው ትልቁ ነገር? ከሱ በፊት ግን የላኩህን ይዘህ መጣህልኝ ቀልበቢስ እኮ ነህ ረስተኸው ይሆናል

ለፍሬም፡- አረ አልረሳሁም እማዬ ይኸው (**ከኪሱ ፖስታ አውጥቶ ይሰጣታል**)

ለዳነች፡- ጎበዝ እኮ ነህ የኔ አንበሳ ተባረክ ትልቅ ደረጃ ድረስልኝ

ያሬድ፡- እንዴ እቴቴ እሱን ብቻ ነው እንዴ የምትመርቂው እኔስ ልጅሽ አይደለሁም? አብረን እኮ ነው ያመጣነው፡፡

ለዳነች፡- ውይ ውይ ያሬድዬ አንተንማ እንዴት እረሳሀለው፤ እድግ በልልኝ፣ ለወግ ለማዕረግ ያብቃህ ተባረክ፤ በሉ አሁን ትልቅ ዜና አለን አላላችሁም ንገሩኛ

ያሬድ፡- ዛሬ ት/ቤት ውጤት ተነገረን

ማከዳ፡- ኤፍሬም ስንተኛ ወጣ?

ለዳነች፡- ያው እንደለመደው 45ኛ ወይ 50ኛ ወጥቶ ይሆናላ፤ ዘንድሮማ ብሶበታል እኮ

ኤፍሬም፡- ኧረ እማዬ በጣም ነው ያሻሻልኩት፤ እኔ ኤፍሬም ወንዱ ልጅሽ ጥሬ፣ ግሬ ላቤን ጠብ አድርጌ፣ ሌተቀን አንብቤ ከ65 ተማሪ 63ኛ ወጣሁልሽ፤ ጀግና አይደለሁ ታዲያ? (**ማከዳ ትስቃለች፣ ያሬድም አንገቱን ደፍቶ በትንሹ ፈገግ ይላል**)

ለዳነች፡- አንበሳ ነህ እንጂ ጎበዝ!! ምነው ያሬዴ አንገትህን ደፋህ ውጤትህ ጥሩ አይደለም እንዴ?

ማከዳ፡- እማዬ ያሬድማ ወይ 1ኛ ወይ 2ኛ ነው ሚወጣው፤

ለዳነች፡- ወይ ውይ ያሬድዬ ምነው አታነብም እንዴ? አይዞህ በቃ ለመጪው ዓመት ታሻሽላለህ እሺ፤ ከወጡ አይቀር ተለቅ ተለቅ ያለውን እንጂ ትንሽ ትንሹንማ ምን ያደርጋል? በሉ ተጫወቱ የተላከልኝን ደብባቤ ላንብብ

ያሬድ፡- አንደኛ እንደወጣህ ለምን አትነገራቸውም? እኔ ልንገራቸው?

ኤፍሬም፡- ባክህ እማዬ 1ኛ ወጣሁ ብላት ደስ አይላትም እሷ የምትፈልገው ተለቅ ተለቅ ያለውን ነው፡፡

(ማከዳ፤ያሬድና ኤፍሬም በማይም መድረኩ ላይ ይጨዋወታሉ አዳነች ጥግ ላይ ሆና የተላከላትን ደብዳቤ ታነባለች ከመድረክ ጀርባ ደብዳቤው ሲነበብ ድምፁ ይሰማል፡፡)

« ውዷ እህቴ እንዴት ነሽልኝ? እኔ አበራ ለጤናዬ በጠም ደህና ነኝ… በጣም የሚገርም እኮ ነው፤ በስንት አመታችን አሁን ላይ መገናኘት ማለት ለኔ በጣም ትልቅ ነገር ነው፤

እህታባ ከሃገር ወደ ሃገር እተዟዟርሽ ስራ እየሰራሽ ቢሆን ነው እንጂ ይሄን ሁሉ ዓመት እንዴት ትጠፊያለሽ? ዋናው አንቺ ሰላም መሆንሽ በቂ ነው፡፡ እህታባ አሁን ላይ ኑሮ በጣም አስቸጋሪ ሆኗል ያልተወደደ ነገር የለም፤ አንድ መኪና ለመግዛት አምስት መቶ ሺህ ይሉሻል፣ አንድ ቤት እንኳን ለመግዛት ሁለት ሚሊየን ብር ያስፈልጋል በጣም ይገርምሻል ብቻ ስንገናኝ ሁሉንም እነግርሻለው፡ እኔ ምልሽ እህታባዬ ሰሞኑን ስራ ቦታ ከባድ ነገር ገጥሞኛል፡ ያው የስራን ነገር ታውቂው የለ… እናም በባንክ ቁጥሬ በቅርብ ቀን የምመልሰው 3ሚሊየን ብር ላኪልኝ፡፡ ባይገርምሽ ልክ እንደተለያየን እኔም ትዳር ይዤ ወንድ ልጅ ወልጃለው ስሙ ያሬድ ይባላል እንዴት አይነት

እኔስ አርሴማን እወዳታለው

ጎበዝ መሰለሽ? ግን የሆነ ዱርዬ ልጅ ገጥሞ ብልሽት ብሏል ጓደኞቹ የእጃቸውን ዋጋ ስለሚያገኙ ብዙ ኢያሰስብሽ፤ ባይገርምሽ የገዛሁለትን ኢይፎን(iphone) ሁለት ወር ሳይጠቀምበት ሸጠው። ኧረ እንዴት ኢይነቱ ኢድርቅ ልጅ መሰለሽ? እናቱ ደግሞ ዘውትር ጠዋት ማታ ህልም ኢየሁ ነው.... እህታባዬ እባክሽ ሳያሳብዱኝ ቶሎ ድረሺልኝ። የብሩን ነገር ግን ኢደራ እሺ... ቻው በቃ

ኤፍሬም፡- እማዬ ማነው?

ሉዳነች፡- አጎትህ ነው፡ ሰላም ብሎአችኋል

ማከዳ፡- እማዬ መቼ ነው አጎታችን የምታስተዋውቂን? ደግሞ የት ነው ሚኖረው?

ሉዳነች፡- ሰሞኑን እናገናኛለነን እሺ እኔም ልፃፍለት ከባድ ችግር ገጥሞኛል ብሎኛል እግዚአብሔር ከችግሩ ይገላግለው፡፡ተነስ እስኪ ወረቀትና እስክሪብቶ ይዘህና፤ ከዚያ ፖስታ ቤት አድርሰህ በጊዜ ትመለሳለህ እሺ እንዳትቆይ፡፡ (***<u>መጋረጃ ይዘጋል</u>***)

ትዕይንት- 4

አባት፡- አየህ ልጄ በፈተና ጊዜ እንኳን እንደፀኑ ናቸው ያሬድ ኤፍሬምን ለመውደድ ኪሱን ሳይሆን ልቡን ነበር የፈለገው ሁለቱንም ፍቅር አስተሳስሯቸዋል

ወጣቱ፡- ከዚያስ አባ ምን ሆኑ?

አባት፡- ከዚያም የተላከውን ፖስታ ለማድረስ ያሬድን ሊጠራው መጣ እንዳጋጣሚ እነያሬድ ቤት ትልቅ ድግስ ተደግሶ ነበር

ወጣቱ፡- የምን ድግስ? የማርያም ወይም የገብርኤል?

አባት፡- የሞት ድግስ ነው፡፡ አቶ አበራ ያንን ምስኪን ብላቴና ሊያስገድል ሁለት ሰዎች ቀጥሮ አሰማርቶ ነበር፤

ወጣቱ፡- ከዚያስ አባቴ ....

(**አበራ መድረኩ ላይ ስልክ ያወራል**)

አበራ፡- ሃሎ ትሰማኛለህ ጉዳዩ በጣም አንገብጋቢ ስለሆነ በፍጹም ከዛሬ ማለፍ የለበትም፡፡ ችግር የለውም ብሩ አያሳስባችሁ አስር ሺህ ብር እከፍላችኋለሁ ከዛሬ ማለፍ የለበትም፡፡..... በጣም ጥሩ ቻው፡፡ (**ስልኩን ይዘጋዋል**) ማነሽ ማርታ! ማርታ አትሰሚም እንዴ? ተኝታ ይሆናል እኮ......ማርታ!!

ማርታ፡- አቤት! ጠራኸኝ ስራ እየሰራሁ ነበር፡፡ በሰላም ነው ግን የፈለከኝ?

አበራ፡- ምን ሰላም አለ/ምን ያልተፈጠረ ነገር አለ? ዛሬ ግግ ፍፃሜው ይሆናል፡በቃ! ከዛሬ ጀምሮ ምንም የሚየያስስንቀኝ ነገር አይኖርም ሃሃሃሃ..... (**የፌዝ ሳቅ ይስቃል**)

ማርታ፡- በስንቱ ተጨንቀህ ትችለዋለህ? ኧረ ባክህ ፈታ በል አንተ ሰው፤ ባይሆን የምነግርህ ትልቅ ነገር አለኝ ትልቅ ነገር?

(**ይደነግጣል**) ም.......ም...ንድነው ትልቅ ነገር?

ማርታ፡- ምነው ደነገጥክሳ?

አበራ፡- አይ ወዲህ ነው፡፡ ምንም አልሆንኩም ንገሪኝ

ማርታ፡- ምን መሰለህ ነገሩ.....

አበራ፡- (**ወሬውን ያቋርጣትና ወደ ዘበኛው ሄዶ....**) ማነህ መኩሪያ ... መኩሪያ

መኩሪያ፡- አቤት ጋሽዬ ጠሩኝ?

አበራ፡- በሩን በደንብ ነቅተህ ጠብቅ ማንንም እንዳታስገባ ሰምተሀል አይደል?

መኩሪያ፡- በደንብ ነው የሰማሁት ማንም ድርሽ አይልም፡፡

እኔስ አርሴማን እወዳታለው

አበራ፡- በጣም ጥሩ፤ ማነው ይኼ ኤፍሬም የሚሉት መናጢ ከመጣ እዚህ ቤት ሁለተኛ ድርሽ እንዳይል ንገረው፤ ሰማህ አይደል ሁለተኛ!!!

መኩሪያ፡- ሄደህ ተኛ? የት ነው ሚተኛው ከኔ ጋር ነው ጋሼዬ?

አበራ፡- አንተ ሰውዬ ችግር አለብህ እንዴ? አትሰማም የትባለውን ማንም ሰው ድርሽ እንዳይል!

መኩሪያ፡- ደራሽ ወሀ! የምን ደራሽ ነው ጋሼዬ?

አበራ፡- አሁንስ ያበዛኸው አልመሰልህም? በቃ ማንም እንዳይገባ!!!!!

መኩሪያ፡- ደግ፤ ማንም አይገባም ወፍ እንኳን ድርሽ አይልም (**አበራ ወደ በት ተመልሶ ይገባል……**)

ማርታ፡- ምንድነው የምትጨቃጨቁት/

አበራ፡- ምን ይኼ ጤና የሌለው ሰውዬ …. ባይሆን እሱን ተይውና ቅድም የጀመርሽውን ትልቅ ነገር ንገሪኝ፤

ማርታ፡- ምን መሰለህ ውዴ …. በዓይነቱ ለየት ያለ ህልም አየሁ፡፡

አበራ፡- ህልም አየሁ?

ማርታ፡- አዎ ህልም አየሁ፡፡

አበራ፡- ማርቲዬ በዚህ ሰዓት ትቀልጃለሽ? ባይሆን ማታ ትነግሪኛለሽ

ማርታ፡- ግድ የለህም አሁን ልንገርህ ስማኝ……

አበራ፡- እሺ እሰማሻለሁ ያሬድን ጥሪው የት ሄዶ ነው/

ማርታ፡- እያጠና ነው እጠራዋለው ***(ወደ ጓዳ ትገባለች…… ኤፍሬም ይመጣል በር ላያ ከመኩሪያ ጋር ይገናኛሉ፡፡)***

መኩሪያ፡-- ወዴት ወዴት? ቁም ብዬሃለው!

ኤፍሬም፡- ምነው መኩሪያዬ ኤፍሬም እኮ ነኝ ያሬድን ፈልጌው ነው፤

መኩሪያ፡- ሬድዮ ፈልጌ ነው? ሬድዮዬንማ አልሰጥህም ደፋር ነህ ባክህ…

ኤፍሬም፡- ኸረ ያሬድን ነው ያልኩህ፡፡

መኩሪያ፡- የለም ብያለው የለም!!! እምቢ ካልክ ግን ማዳመጫህን በዚህ ዱላ ብ …….

ኤፍሬም፡- በል አሁን ጥራልኝ፡ (**ከኪሱ ከረሜላ ይሰጠዋል**)

መኩሪያ፡- ከረሜላ! ኧረግ ኧረግ ተባረክ፡፡ እዚሁ ጠብቀኝ እጠራልሃለው፡፡ግን ወደ ውስጥ እንዳትገባ……

ኤፍሬም፡- እሺ አልገባም ቶሎ በል ጥራልኝ፤

(***መኩሪያ ወደ ውስጥ ያሬድን ሊጠራ ይገባል ቤት ውስጥ አበራን ያገኘዋል***)

እኔስ አርሴማን እወዳታለው

መኩሪያ፡- ማነህ ያሬድ.... ያሬዶ... ጋሽዬ ያሬድን ሰው ይፈልግሀል በሉት፡

አበራ፡- ማነው ሚፈልገው?

መኩሪያ፡- ኤፊዬ ነው

አበራ፡- ማን አልከኝ?

መኩሪያ፡- ኤፍሬም ነው ጋሼ፡ ላስገባው?

አበራ፡- ኤ ... ኤ ...ፍሬም? ምን አልክ አንተ ደደብ? ማንም እንዳይገባ አላልኩህም አይኑን ማየት አልፈልግም አሁኑኑ አስወጣልኝ!!

መኩሪያ፡- አይኔ ውስጥ ትንኝ ገባ አውጣልኝ/

አበራ፡- አይን አባትህ ይውጣ ያንን መናጢ ማየት አልፈልግም አባርልኝ

መኩሪያ፡- እሺ..... ደግ ... ደግ .... አይገባም ችግር የለውም ይቀመጡ በቃ... (**መኩሪያ ወደ ውጪ ወጥቶ ....**)

መኩሪያ፡- አንተ ጥላ ቢስ አልሄድክም እንዴ? (**ሽለላና ቀረርቶ ይደረድራል**)

ኤፍሬም፡- ምነው የለም እንዴ?.... መኩሪያ ተረጋጋ እንጂ፤

መኩሪያ፡- እምቢ አልረጋጋም ሂድ ከዚህ ብዬሀለው... በእጄ ሰበብ እንዳትሆንብኝ፡፡

ያሬድ፡- አባዬ ሰላም ነው፡፡ ያሬድ ስትሉ ሰማሁ ምነው ፈለጋችሁኝ?

አበራ፡- አዎ እኔ ነኝ የፈለኩህ፡፡ እንዴት ነህ ትምህርት አሪፍ ነው?

ያሬድ፡- ደህና ነኝ አባዬ ትምህርት በጣም ጥሩ ነው ዘንድሮ 2ኛ ነው የወጣሁት፣ ኤፍሬም ደግሞ አንደኛ ነው የወጣው፤

አበራ፡- ምን አልክ አንተ??? (**በማዘንና በቁጭት አንገቱ ይደፋል**)

ያሬድ፡- ምነው አባዬ ቅር አለህ እንዴ?

አበራ፡- እንዴት ነው ቅር የማይለኝ? እንዴት ሁለተኛ ትወጣለ? /አንደኛ መውጣት ሲገባህ እንዴት.... እንዴት?

ያሬድ፡- ኧረ አባዬ በቃ ተረጋጋ በሚቀጥለው ሴሚስተር አሻሽላለሁ፡፡

አበራ፡- አሁን ተወኝ!! ያ ኤፍሬም የሚሉት መናጢ እያለ እንዴት ሁለተኛ አትወጣ??! ጉድ እኮ ነው....

ማርታ፡- ምንድነው ጭቅጭቅ? ያሬድ ምንድነው ምን አጠፋህ ደግሞ?

አበራ፡- ወይኔ አበራ ተዋረድኩልሽ ጉድ ሆንኩልሽ፤

ማርታ፡- ኧረ ምንድነው በጭንቀት ልትገሉኝ ነው እንዴ?

አበራ፡- ተይው! አንቺ ምንም አትጨነቂ እኔ እራሴ አስተካክለዋለው!!!

ማርታ፡- በቃ እሺ አሁን ተረጋጋ... ቀድም የጀመርነውን ትልቅ ጨዋታ እንቀጥል አይደል...

አበራ፡- እሺ ቀጥዬ ምንድነው? (**በመሀል የአበራ ስልክ ይጠራል ...**) ሄሎ..... ስራው አለቀ?.... ምን?..... አመለጠ? እንዴት ብሎ ነው

እኔስ አርሴማን እወዳታለው

ሚያመልጣችሁ? ፈልጋችሁ እንዳዘዝኳችሁ ፈፅሙ ...(ይዘጋዋል)

ያሬድ፡- ምንድነው ያመለጠው? ምንድነው ሚፈፅመው?

አበራ፡- አይ የስራ ጉዳይ ነው

ማርታ፡- እስቲ አታቋርጡኝ በናታችሁ (ህልሙን ስትቀጥል ስትል ኤፍሬም ሰውነቱ በደም ተለውሶ ከውጪ ይገባል.... በሩ ጋር ሲደርስ ድፍት ብሎ ይወድቃል)

መኩሪያ፡- ኧረግ...... ኧረግ.... ኡ...ኡ... ኡ .... ጋሼ ጋሼ ጉድ ሆነናል **(ያሬድ አበራና ማርታ ደነግጠው ይወጣሉ ...)**

ያሬድ፡- ምንድነው? ምንድነው? .... ኤፍሬም... ኡ ... ኡ....... ኡኡኡ..... ወይኔ ጓደኛዬ ምን ሆንክብኝ?

ኤፍሬም፡- ያ..ሬ..ድ.. ይኼን ፖስታ ወስደህ ፖስታ ቤት ... አስገባልኝ ... እህ........ እህ .... እማዬን እና ማ...ክ....ዳ.....ን አደራ.... እሺ

(ፖስታ ይሰጠዋል ያሬድ ሊቀበለው ሲል አበራ ቀምቶ ይወስደውና ያነበዋል ያሬድ ኤፍሬምን አቅፎ ያለቅሳል ደብዳቤው ከመድረክ ጀርባ ይነበባል)

« ውድ ወንድሜ እንዴት እንዴት ነህልኝ፤ በቀደም የላክልኝ ደብዳቤ ደርሶኛል አመሰግናለው... ወንድምአለም አግኝቶ ማጣት ምንኛ ከፉ መሰለህ እኔ እህትህ በለቤቴ ከሞተ በኋላ ሀብት ንብረታችን በባንክ እዳ ተይዞ ተወርሷል እጃችን ላይ እንኳን 3ሚሊየን ብር 3 ብር የለንም፤ አበራ ከድሮ ፀባይህ አሁን ትሻላለህ ብዬ አስቤ ነበር እንድንገናኝ የፈለኩት ግን አንተ ያው ነህ ለሰዎች የማትራራ ነህ፤ አለስተዋልከ ይሆናል እንጂ ከእናንተ ቤት ጀርባ ደሳሳ ጎጆ ዉስጥ ከሁለቱም ልጆቼ ጋር እየኖርኩ እከታተልህ ነበር፡ ከዛሬ ነገ ትሻላለህ በማለት ብዙ ታገስኩህ፤ አሁን ግን በቃ! ማትሻሻል ሰው ስለሆነኩ ከነገ ጀምሮ አንተ ባለፍክበት ላላልፍ ወስኛለው፤ ልጄ ኤፍሬምም ቢሆን ድጋሚ የያሬድን አይን አያይም፣ በጨዋ ደንብ ተንከባክቤ ያሳደኩት ልጄ ያንተን ልጅ የሚያበላሽ ከሆነ ነገዉኑ ከተማውን ስለምንለቅ አታስብ፤ ለማንኛውም ግን ያሬድ ማለት ለኔ ከኤፍሬም አኩል የማየው ልጄ ነው ምነለባት አኛን ቢያጣንና ቢጨነቅ ከታች በጻፍኩት ስልክ ደውለህ አገናኝን ካልሆነ እንዳትደውል፤ ወንድምአለም ባለህበት ሁሉ መልካሙን እመኝልሃለው ያንተው እህት አዳነች...

(አበራ አንብቦ ሲጨርሰስ ያለቅሳል)

አበራ፡- ኡ....ኡ ... አንቡላንስ ጥሩልኝ .... ወይኔ ጉዴ.... አረ ቶሎ በሉ ያሬድ ቶሎ በል!!! .... ማርታ ጨርቅ ይዘሽ ነይ!!! .... ኡ ... ኡ ...

መጋረጃ ይዘጋል

ትዕይንት 5

አበራ፡- በሰዎችና በመላዕክት ልሳን ተናግሬ

ቃላት ገጣጥሜ ሀረግን ቀምሬ

እምነትን ከምግባር ጋር አንድ ላይ ደምሬ፤

ማርታ፡- ምስጢር አዋቂም ብትሆን ትንቢት ተናጋሪ

ሊቀ ሊቃውንት ጠበብት ምሁር አማካሪ፤

መኩሪያ፡- በ300 ሰራዊት ህዝቤን ከጠላት ባድን

የጀግኖች ጀግና ተብዬ በጠጠረ ትልቁን የምገድል

ልበ ደንዳና ፈርጣማ ከአንበሳ የምታገል፤

ማከዳ፡- ሺህ እንባ አፍስሼ እግሩን በሽቶ ባጥበው

ልብሱን በዕምነት ነክቼ ደሜን ቢያቆመው፤

አዳነች፡- እንደ ሀዋርያቱ ብጠራም ጀልባ መረቤን ጥዬ

ከአፅናፍ አፅናፍ ብሰብክ ሞልቶ ቢፈስ ማድጋዬ፤

ኤፍሬም፡- እንደ ቶማስ ተገፍፌ እንደ ጴጥሮስ ቁልቁል

ሺህ መከራ ቢያልፍ ሰማዕትነት ብቀበል

ፍቅር ከሌለኝ ከንቱ ነኝ

ፍቅር ከሌለኝ ባዶ ነኝ

ያሬድ፡- ፍቅር ይታገሳል

ቸርነት ያደርጋል

ልብን ሀሴት ሞልቶ ሰላምን ይሰጣል

ፍቅር ሁሉን ያምናል

ሁሉን ተስፋ ያደርጋል

በፈተና ጊዜ በእግዚአብሔር ይጸናል፡፡

እኔስ አርሴማን እወዳታለው

አባት፡- ልጄ አሁንስ ከነገርኩህ ታሪክ በደንብ የተማርክ ይመስለኛል

ወጣቱ፡- ኧረ በደንብ ተምሬያለው፤

አባት፡- በጣም ጥሩ፤ ለጓደኝነት መሰረቱ ፍቅር ነው፣ ለፍቅር መሰረቱ ደግሞ እግዚአብሔር ነው.... ስለዚህ ልጄ አሁኑኑ ሄደህ የተጣላኸውን ጓደኛህን ይቅርታ በለው፤ ይቅርታ ማደረግ ታላቅነት ነው፤ በይቅርታ ዉስጥ ፍቅር አለና! በል ተነስ እኔም የምሄድበት ቦታ አለኝ ሌላ ጊዜ እንገናኛለን፤ ደህና ሰንብት፡፡

ተፈፀመ

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



ድርሰት፡- ዲ/ን እዮብ ክንፈ (ፍቅረ ማርያም)
ቀን - 06/09/09 ዓ.ም
09-25-50-63-72

እኔስ አርሴማን እወዳታለው